# ስብሐት ለአምላክ

## 2ኛ መጽሐፍ

አዘጋጅ ፦ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የወንጌል አገልግሎት መምሪያ

አሳታሚ ፦

መካነ ኢየሱስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል

አዲስ አበባ
1 9 8 7

ጉልበት መጠጊያ ኃይላቸው።
የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፣ ... ።

3፤ በሙሴ ውስጥ ሆነህ የሠራህ፣
የኤልያስ አምላክ ወዴት ነህ።
አልረሳንም ከቶ ተስፋህን፣
እንደምትሰጠን ኃይልህን።
የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፣ ... ።

4፤ መንገዳቸው ተከበ በባሕር፣
በጣም ተቸገሩ ለመሻገር።
ሙሴ ወደ አንተ ሲጮህ ሲያለቅስ ሳለ፣
የኤርትራ ባሕር ተከፈለ።
የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፣ ... ።

5፤ ከዚያም ተሻገሩ በደስታ፣
አንተ ሆንክላቸው መከታ።
ማነው እንዳንተ ታላቅ ንጉሥ፣
እኛንም አትርሳን እግዚአብሔር ሆይ፣
ተነሥ።
የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፣ ... ።

ቃላትና ዜማ በመሠረት ጽጌ።

## መዝሙር 425።

ብርሃኔ ነህ ጌታ የሕይወቴ ዋልታ፣
የነፍሴ እረኛ የመኖሬ አለኝታ።
ብርሃኔ ነህ ጌታ የሕይወቴ ዋልታ፣
የነፍሴ እረኛ የመኖሬ አለኝታ።

1፤ ፍላጎቴን አስተውል ተረዳ ሐሳቤን፣
መንገዶቼን አቅና መርምር አካሄዴን።
ብርሃኔ ነህ ጌታ ... ።

2፤ ተመልከት አምላኬ ደካማ ጎኔን፣
የልቤን ስብራት ሁለንተናዬን።
ብርሃኔ ነህ ጌታ ... ።

3፤ አንተ ነህና የሱስ የነፍሴ መጽናኛ፣
አታገኝም ሌላ ሕይወቴ መዳኛ።
ብርሃኔ ነህ ጌታ ... ።

4፤ ፍጠርልኝ ጌታ የልቦናን ጆሮ፣
ለግሠኝ አምላኬ አስተዋይ አእምሮ።
ብርሃኔ ነህ ጌታ ... ።

ቃላትና ዜማ በገብረ ጻድቅ አዲቶ።

## መዝሙር 426።

አስተምረኝ ጌታዬ ሆይ፣
አስተካክላት ሕይወቴን።
መንገዴን ሁሉ ስራመድ፣
አንተ ከኔ ጋር ሁን።

1፤ በመንገዴ ላይ ሳለሁ ፍጹም እንዳልፈራ፣
የኤልያስ አምላክ ሁንልኝ ከኔ ጋራ።
አስተምረኝ ... ።

2፤ ሙሴን በምድረ በዳ በቃልህ ያጸናህ፣
አበርታኝ ልጅህን እኔም እንድከተልህ።
አስተምረኝ ... ።

3፤ ለጳውሎስ እንደ ሰጠህ ብርታትና ኃይልህን፣
ልጅህንም አበርታው ካንተ ጋር እንዲሆን።
አስተምረኝ ... ።

4፤ ስራመድ በጉዞዬ ላይ አንተ መሪዬ ሁነኝ፣
በመንገዴ ላይ ሁሉ ጸጋህ አይለየኝ።
አስተምረኝ ... ።

ቃላትና ዜማ በአባተ ደምሴ።

## መዝሙር 427።

ምራን እረኛችን ኢየሱስ ተስፋችን፣
ጸንተን እስክምንደርስ በሰማይ ቤታችን።
ምራን እረኛችን ኢየሱስ ተስፋችን፣
ጸንተን እስክምንደርስ በሰማይ ቤታችን።

1፤ ትርጉም ያለው ኑሮ መኖር አስተምረን፣
የሰላሙ ንጉሥ ንገሥ በሕይወታችን።
ምራን እረኛችን ... ።

2፤ ውዱ አምላካችን አንተ ነህ መሪያችን፣
ጥበቃህ አይለየን ሲዝል ጉልበታችን።
ምራን እረኛችን ... ።

3፤ ስንፈራ ስንደክም ስንተክዝ ስናዝን፣
ጌታ ሆይ፣ በመንፈስህ አበርታን አጽናናን።
ምራን እረኛችን ... ።

4፤ ጠውልገን እንዳንቀር ሙላን በባርኮትህ፣
አለምልመን በጸጋህ አቁመን ለክብርህ።
ምራን እረኛችን ... ።

2፤ በኃጢአት ቍስል ብትማቅቅም፥
በስሜ ካመንክ ፍጹም አትወድቅም።
ስለሚመለስ ጌታ ከሰማይ፥
መብራትህ ይብራ ላለምም ይታይ።
ተራመድ . . . ።

3፤ አትሞኝ ከቶ ባለም ደስታ፥
ስለማታገኝ የሕይወትን ፋታ።
መቅረዝህ ይብራ ቆም ተዘጋጅተህ፥
ጌታ ሲመለስ ትነጠቃለህ።
ተራመድ . . . ።

4፤ ቋሚ ጓደኛ ስላለህ የሱስ፥
በእምነት ተጋደል በተስፋ ገሥግሥ።
ዓለምን አትይ ማብለጭለጩንም፥
ተስፋ ከመቍረጥ አታድንህም።
ተራመድ . . . ።

ቃላትና ዜማ በሰብስቤ መኰንን።

